PANORAMA # 3

# የትዝብት ዕይታ

## ለእኛ ያልሆነች ሀገር ትበጣጠስ

## ለእኛ ያልሆነ ድርጅት ይፈረካከስ

ድርጅትንና ሀገርን በአንድ ሚዛን ማስቀመጥ ፈጽሞ የማይቻልና የማይገባ መሆኑ የታወቀ ቢሆኑም፥ ሁለቱም በየደረጃቸው አስፈላጊ መሆናቸው ግን የሚያከራክር አይደለም። ሀገር መተኪያ የለለው፥ በአማራጭ የማይቀመጥ፥ ለይደር የማይተላለፍ፥ ለአደራ የማይሰጥ ፥ለጥቅም የማይለወጥ፥ ለሀሴት የማይሸጥ መሆኑ ማነኛውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ከልብ የሚያምንበት መሠረታዊ ሀቅ ነው። የሀገርን ማንነትና ምንነት ለመግለፅ፥ ደራስያን፥ የሃይማኖት መሪዎች፥ የሥነ መንግሥት ጠበብቶች፥ የታሪክ መዝጋቢዎች፥ የመልከዓ ምድር ባለሙያዎች ወዘተረፈ በዘመናት እንደየሙያቸው የገለፁት በመሆኑ፥ እኛ ወደ ዝርዝር ሁኔታ ለመግባት የዚች አጭር መጣጥፍ ውሱንነት አይፈቅድልንም።

ብቻ አንድ ነገር አስመረን ማልፍ ግን እንወዳለን። ይኸውም፥እኛ ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የምንያቸው በአማራጭ አይደለም። የምንታገለውም ሁለት ባላዎች የዘን አንዱ ሲሰበር በሌላው ተመርኩዘን አይደለም። የኛ የትግል መነሻና መድረሻችን ኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝቦቿ ናቸው። የድርጅታችን አልፋና ኦሜጋም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እየታገሉ መሰዋት ብቻ ነው። ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ጥበጣጠስ የሚለው ቋንቋ የነ ወያኔና የመሰሎቻቸው መፈክር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ ስለድርጅት ምንነትና ጠቃሚነት በሚነገርበት ወቅት፥ ከሁሉ አስቀድሞ ሊታወቅ የሚገባው ቁም ነገር፥ የትግል ድርጅት የተመሠረተው፥ ብሔራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅና ሕዝብን ከአምባገነን ገዥዎች ነፃ ለመውጣት የሚያስችል መተኪያ የለለው ዓይነተኛ የትግል መሳሪያ መሆኑ ነው። ድርጅት የሚመሠረተውና ሊጫወትም የሚጠበቅበት ሚና፥ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም አገልግሎት እንዲያከናውን መሆኑ ነው። “ሸማ እንደ ፈርጁ” እንዲሉ፥ የሁለቱም ምንነት የተለያየየ ቢሆንም፥ ድርጅት ለሀገር የሚሰጠው ጥቅም ደግሞ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም። በዚህ ረድፍና ንፅፅር፥ ድርጅት ስንል የፖለቲካ ድርጅት ማለታችን እንጅ፥ ትርጉሙ ከዚህ አገላለጽ ሰፋ ብሎ ሲታይ ግን፥ የተለያዩ ተቋማትንም የሚያጠቃልል ይሆናል። ታዲያ የተቋማትን ጉዳይ ስናነሳ፥ ልዩ ልዩ ግልጋሎትና ጠቀሜታ ያላቸውን ሁሉ ማካተት ይቻላል። የንግድ፥ የማኅበራዊ፥ የስፖርት፥ የእርሻ፥ የመጓጓዣ፥ የሃይማኖት፥ እና የመሳሰሉት ተቋማት ሁሉ በድርጅት ረድፍ የሚሰለፉ ይሆናሉ። ሁሉም እንደ አመሰራረታቸው የየራሳቸው አገልግሎት፥ ተልዕኮና ሚና አላቸው። ጠቃሚነታቸውም እንደዚሁ የተለያየ ነው። ሁሉም ቢከማቹ ግን ሀገርን አይተኩም። ሀገር መጀመሪያ፥ ድርጅት ደግሞ ሀገርን ለማገልገል የሚመሰረት ነው። በመሆኑም የኢሕአፓ አባላትም፥ ሀገራቸውን በድርጅት አይተኩም። ድርጅታቸው ግን የትግል መሳሪያ መሆኑን ያምናሉ። ስለሆነም ይወዱታል፥ ይጠብቁታል፥ ያጠናክሩታል እንጅ፥ ፀሀይ በበረቀ ጀምበር በጠለቀ ቁጥር እየጣሉት አይሄዱም።

ከሁሉ በፊትና ለማነኛም ጉዳይ መሠረቱ ሀገር መሆኑ ባይካድም፥ ሁሉም ዓይነት ድርጅቶች ደግሞ ሊያገለግሉ የሚመሠረቱት ሀገርንና ሕዝብን ለመጥቀም እንደሆነ መተንተን የሚያስፈልግ አይመስልንም። ከዚህ ሀቅ ከተነሳን ዘንዳ ፥ በዚህ ርዕሳችን

በስፋት ልናተኩርበት የምንሻው በፖለቲካ ድርጅት ምንነት ላይ ይሆናል፡፡ የሀገር መሪም ይሁን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ከሁሉ በፊት ሊገነዘቡት የሚገባቸው፥ የእነርሱ በመሪነት ቦታ መገኘት፥ ሚናቸውን፥ ተልዕኳቸውንና ብሎም ጠቀሜታቸውን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ/ ዙሪያ ብቻ የሚሽከረከር መሆኑን መረዳት እንዳለባቸው ነው፡፡ ሀገር የሚመራው፥ ሕዝብን ለማገልገል፥ የድርጅት መሪዎች ደግሞ የድርጅትን ዓላማና ራዕይ ለማራመድ እንጅ፥ በቦታው በመገኘታቸው ብቻ የራሳቸውን ክብርና ከንቱ ውዳሴ፥ ጥቅምና ፍላጎት ለማራመድ አይደለም፡፡ እኔ ከሌለሁ ሀገርና ድርጅት ሊኖር አይችልም ከሚል የቀን ቅዠት እራሳቸውን ካላላቀቁ፥ ሀገርም ሆኑ ድርጅት ዕድገትና መሻሻል አያገኙም፡፡ በተፃፃሪው ግን እየጫጩና እየከሰሙ ይሄዳሉ፡፡ ሀገርና ድርጅት ከሚጫጩና ከሚከስሙ፥ አክሳሚዎቹ ከስመው ቢቀሩ መቶ ጊዜ ይመረጣል፡፡ “ የዋርካ ዛፍ፥ ፍሬ ማፍራት ለአዕዋፋቱ እንጅ ዛፉን አይጠቅመውም ” የሚባለው ይትበኃል፥ በመሪዎችና በሀገር መካከል ሊኖር ለሚችለው አባባል ሊሰራ አይችልም፡፡ ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ ያልተገነዘበ ማነኛውም መሪ፥ ፈጠነም ዘገየ፥ በሕዝብና በድርጅት አባላት ኃይል ተሽቀንጥሮ እንደሚወገድ ማወቅ ብልህነት ነው፡፡ ይህ ብልህነት ግን በሀገራችን የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ብዙ ጊዜ የታየና የተሰማ አይመስልም፡፡

በዓለም ካሉት የመንግሥታት መንበረ -ሥልጣናት ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ ጣፋጭና አትልቀቁኝ የሚል ወንበር ያለ አይመስልም፡፡ በወንበሯ ላይ የተቀመጠ ሁሉ፥ ወንበሯን የሚለቃት፥ ወይ ተዋርዶና ተገፍትሮ፥ አለዚያ ደግሞ ተባሮና ሸሽቶ ነው፡፡ ሥልጣኗን ሙጭጭ ብሎ ከያዛት ወደ ከርሰ መቃብሩ ይወርዳታል እንጅ፥ ተወዶና ተከብሮ ሊለቅ አይፈልግም፡፡ አይችልምም፡፡ “ ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል” እየሆነባቸው ነው መስል፥ በክብርና በግርማ ሞገስ ከሥልጣናቸው አይወርዱም፥ የኢትዮጵያ ገዥዎች፡፡ ይህ ክስተት በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች በሚገኙ መሪዎች ያልተለመደ ባይሆንም፥ በኢትዮጵያ ግን በሚያስገርም መልኩ እንደ ባህል ተቆጥሮ ስለሚታይ በመሪዎች በኩል ዕድሜ ልካቸውን በሥልጣን ቢቆዩ ጭራሽ ጎሊናቸው የሚቆጠቁጣቸውና የሚያስቸግራቸው አይደለም፡፡

ከዚህም አልፎ ተርፎ፥በሀገራችን ያለውን ሁኔታ ስንታዘብ፥ እስከዛሬ ድረስ አንድ መፍትሄ ሊገኝለት ያልቻለ የመሪነት በሽታ አለ፡፡ ”ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ” ከሚለው ከወያኔ አሳፋሪና ራስ ወዳድ ድርጊት ጀምሮ፥ ድርጅቱን እኛ በዘለዓለማዊ መልኩ ካልተቆጣጠርነው፥ አፈራርሰንው እንሄዳለን እስከሚለው ውንብድና ድረስ ያለውን ነቀርሳ ስናይ፥ ይህች ያልታደለች ሀገርና ዜጎቿ፥ የቱን ያህል ዴሞክራሲያዊ መሪ እንደሚያስፈልጋቸው ያስረዳል፡፡ መልካም የሀገር መሪዎች ሊዉጡ የሚችሉት ከሕዝብ መካከል እንደመሆኑ፥ የድርጅት መሪዎችም ሊገኙ የሚችሉት በንቃተ-ኅሊና ከበቁ-ከነቁ አባላት መካከል መሆኑ አንድና ሁለት አይባልም፡፡ ሀገር ያለ መሪ መኖር ይችል እንደሁ እንጅ፥ መሪ ያለ ሕዝብ ግን በምንም ምክንያት ሊኖር እንደማይችል ሊታወቅ ይገባዋል፡፡

በሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲ ጉዳይ ከተነሳ፥ ለዓብነት ኢሕአፓን መጥቀስ የሚቻል ይመስለናል፡፡ በኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት የመንግሥት ታሪክ ሂደት፥ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲ በመሆን የበኩር ሚናውን ሊጫወት የበቃው፥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ለመሆኑ፥ የሀገራችን የፖለቲካ ዜና መዋዕል መዝግቦታል፡፡ ይህም በመሆኑ፥ የፖለቲካ ድርጅት አንጋፋነቱን ማንም ሊነፍገው አይችልም፡፡ ከዚህ ዕውነታ በመነሳት፥ የሀገራችን የፖሊቲካ ታዛቢዎችና ተንታኞች፥ ኢሕአፓን በጣምራ ባኅርይ ዕይታ ይገመግሙታል፥ ይተነትኑታል፡፡ ለዚህ አመለካከታቸው፥ ሁለት ዓይነተኛ የታሪክ ማዕዘኖችን መሠረት ያደርጋሉ፡፡

በአንድ በኩል፥ ኢሕአፓ፥ በሀገራችን የፖለቲካ መልከዓ-ምድር የመጀመሪያ ፓርቲ በመሆኑ ምክንያት በፖለቲካ ድርጅትነትና አደረጃጀት፥ አሰራርና አወቃቀር፥ የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት፥ የትግል ስልትና ስትራተጂ በመንደፍ፥ ብሄራዊ ራዕይን በማሳየት፥ ሕዝብን በመቀስቀስ፥ በማደረጀትና በማስተማር፥ የአምባገነን ሥርዓትን፥ ቢቻል በሰላም

ትግል ማስወገድ፥ ያ ካልሆነ ደግሞ ዘርፈ-ብዙ ትግል አካሄዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማምጣት እንደሚቻል በተግባርና በመሥዋዕት አሳይቷል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ታሪክ ፥ መንግሥት አይወቀስ፥ አይከሰስ፥ አይደፈር፥ የሚለውን ባህላዊ ዕምነት እንዲሻር በማድረግ፥ ሕዝብን የሚበድል የመንግሥት ሥርዓትና በሕዝብ የተወገዘ መሪ፥ ሊወድቅ ብሎም፥ በታሪክና በህግ ፊት ሊፈረድበት እንደሚችል በተጨባጭ አሳይቷል፡፡ በዚህም የረጅም ዓመታት የትግል ታሪኩ እልፍ አዕላፍ አባላቱ እንደተሰዉ፥ ከፍተኛ የአካልና የመንፈስ ስቃይ እንደተቀበሉ፥ ወህኒ እንደወረዱ፥ እንደተጋዙ፥ እንደ ተሰደዱና ታሪካቸውንም በኢትዮጵያ የታሪክ ምዕራፍ በወርቅ ቀለም እንዳስመዘገቡ ይተረካል፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ፥ ላለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብና አዕምሮ የተለይ ቦታ እንዲሰጠው መደረጉ ነው፡፡ ይህም ኢሕአፓን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ተቋም ያደርገዋል፡፡ ይህ የተቋምነት ገጽታው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሀብትና ዘለዓለማዊ የሆነ ብሄራዊ ቅርስ ሆኖ ይኖራል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና ስትራተጂያዊ ዓላማ ሲል በመነሳት ሲታገል በፈፀመው ስህተትም፥ የተሳወለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲፈርድበትና ሲፈርድለት፥ ሁሉንም በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ ሆኖ ነው፡፡ ይህንንም ሲቀበል፥ በኢትዮጵያ ሕዝብና በታሪክ ፍርድ ትክክለኛነት በሙሉ ልብነት በመተማመንም ጭምር ነው፡፡

የኢሕአፓን ሁለተኛ ገፅታና ስብዕና ለመገምገም የሚቻለው/ የሚገባውም በፖለቲካ ፓርቲነቱ ወይም ድርጅትነቱ ይሆናል፡፡ እንደ ማነኛው ሀገር የፖለቲካ ፓርቲ፥ ኢሕአፓም የራሱ የሆነ ሀገራዊ ማንነትና ሰብዕና፥ ታሪካዊ መነሻና መድረሻ፥ አፈጣጠር፥ ሂደትና ዕድገት፥ በኀርይም ሆነ ተግባር፥ እንደዚሁም ፕሮግራም፥ ዓላማና ራዕይ አለው፡፡ ኢትዮጵያዊ በኀርዩን፥ ታሪኩንና ባኅሉን መሠረት በማድረግ፥ ዓላማውን ከራዕዩ፥ ፕሮግራሙን ከብሔራዊ ተስፋው ጋር በማጣጣምና በማስተባበር፥ በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ እንዲፈጠር ይታገላል፡፡ በኢትዮጵያ ሀገራችን የመጨረሻው ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ያው እራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ከልብ ስለሚያምን፤ የሕዝቡ የሥልጣን ልዕልና የሚፈጠርበትንና የሚመቻችበትን ብሎም አሳታፊ ዲሞክራሲ መሠረት የሚጣልበትንና ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማምጣት የቅድሚያ የትግል አጀንዳው በመድረግ ይታገላል፡፡

በዕርግጥም፥ በሀገራችን የህግ የበላይነት ሰፍኖ፥ የሕዝቡም ዲሞክራሲያዊ መብትና ነፃነት ተከብሮ፥ ብሔራዊ የምርጫ ውድድር ሲከናወን፥ ኢሕአፓም የራሱን ፕሮግራም፥ ራዕይና አጀንዳ ለሕዝብ አቅርቦ የሕዝቡን ዕምነትና ድጋፍ ካገኘና ከተመረጠ ፥ የሀገሪቱ ህገ መንግሥት በሚፈቅደው ድንጋጌና ሥነሥርዓት መሠረት፥ የመረጠውን ሕዝብ በትጋትና በታማኝነት የማገልገል ዕድል ይኖረዋል፡፡ በውድድሩ ውስጥ በመግባት የሕዝቡን ምርጫ ካላገኘ ደግሞ፥ አለመመረጡን በፀጋ ተቀብሎ፥ በተቃዋሚነት የፖለቲካ ፓርቲ ሚናውን ለመጫወት ዝግጁ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ የዴሞክራሲን ደንብና ሥርዓት፥ መብትና ግዴታ፥ ኃላፊነትንና ተገዥነትን ተቀብሎ፥ የፓርቲ ህይወቱን በሰላማዊ መንገድ ይመራል፡፡ ይህ ደግሞ የኢሕአፓን የፖለቲካ ፓርቲ ሰብዕናም ሆነ ባኅርይ የሚያሳይበት የማንነቱ መግለጫ ይሆናል፡፡

እንግዲህ ኢሕአፓ እነኚህን ሁለት ባኅርያትና ማንነት አንግቦ ሲገኝ፥ ማለትም፥ በአንድ ገፅታዉ፥ እንደ ብሔራዊ ተቋም፥ በሌላ ገፅታው ደግሞ፥ እንደ ፖለቲካ ፓርቲነቱ ማንነቱን በማረጋገጡ፥ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከአ-ምድርና የታሪክ ማኅደር ውስጥ የተለየ ያደረገዋል ብለው አባላቱ ያምናሉ፡፡ይህም ዕምነት የመነጨው፥ በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢሕአፓ አባላት መካከል በመሥዋዕት የተሳሰረ፥ ብሎም ታሪክና ዘመን ሊሽረው የማይችል ብሔራዊ ቃል ኪዳን ስላለ ነው፡፡ ይህ አባባል ፖለቲካዊ ነባቢት ወይም ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሳይሆን፥ አባላቱ፥ ኢትዮጵያ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን ከልብ

ስለሚያፈቅሩ ብቻ ነው፡፡  ሰውም ሆነ ድርጅት፥ ፍቅሩን ለመግለፅ፥ ህይወትን አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ሌላ ምን ሊያደርግ ይችላል? ይህ ብሔራዊና ሕዝባዊ ፍቅር ላለፉት ሠላሳ አምስት የትግል ዓመታት አይከፍሉ መሥዋዕት በመክፈል የተመሠከረ ነው፡፡

ለዚህም ነው፥ ለእኛ ለወያኔዎቹ ያለሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ፥ ወይም ደግሞ ድርጅቱን እኛ ብቻ መቆጣጠር ካልቻልን ፍርስርሱ ይውጣ የሚሉትን ከንቱዎች አጥብቀን የምንቃወማቸው፥ የምንታገላቸውም፡፡  ለሁሉም ግን ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለታሪክ እንሰጠዋለን!!!!!!